# ሐቁ ተሰደደ!



ከሀና ሰመረ (ኖርዌይ)
hannasemere@yahoo.com

ትናንትሽን ከአድማስ ማዶ
ባዕድ ሀገር ማንስ ወዶ
እኔና እናንተ እኮ ከአመታት በፊት
በታሪክ በሃይማኖት በባህል በትውፊት
በጋሻና በጦር ጀግኖች ባለሀገር
የአንድ አያቶች ዘር የአንድ አፈር ሰፈር
ግና ዛሬን ይኸው ይከፋፍሉናል
እራስን ከፍ አርገው ትንሾች ይሉናል
በስልጣን ከፍ ከፍ
በሃብትም ከፍ ከፍ
የወደቁ ለታ ማንነት እንዳይተርፍ
ትንሹ ነብዩ በጥይት ተገድሎ ያላንዳች ጥፋቱ
ያለ ፍትህ ታስሮ ስንቱ ወገኔ ሞቶ ወጣት አዛውንቱ
ይሄ ሁሉ ጥፋት ፍትህ አልባነቱ
የየኔ ሰው ገብሬ በእሳት መሞቱ
የሐረሩን እንቡጥ ተስፋችን የነገው
ቀጥቅጥጠው ገደሉት ባልዋለበት ውለው
እስክንድር ፤ አንዱአለም ፤ ናትናኤል ፤ ርዕዮት አለሙ
ያለ ምንም በደል በግፍ የታሰረው ክርስቲያን ሙስሊሙ
ፍትህ ቢጎድልበት ተገፍትሮ የወጣው
በሳውዲ አረቢያ ደሙ ለፈሰሰው
የወገኔን እንባ ወገኑ አበሰው
ይብላኝ ለወያኔ ቀኑ ለደረሰው
ማዳመጥ አይሻ ተቃዋሚ አፍርሶ
እኔ ብቻ አዋቂ ጭራሽ ተኮፍሶ
በአኬልዳማ ሽብር ህዝብ እያሳደደ
ውሸት ተደላድሎ ሐቁ ተሰደደ::
ምንድን ነው ነፃነት?
ባርነት ምን ሲባል ብለው የታገሉት
ለነፃነት ብለው ህዝብ ላይ ጉብ ያሉት
አዋቂ ነን ብለው ታሪክ ያጎደፉት
ከዚህ መልስ ኦሮሞ
ከዚያ መልስ ጋሞ
ከዚህ መልስ ሲዳማ
ከዚያ መልስ ኩናማ
አንድነት በትነው
ህጉን አፈራርሰው
ክፍፍልን ዘርተው
ይሄ ነው ነፃነት ስንቱ የሞተለት?
ይበቃል ከእንግዲህ ጨለማ አንፈልግም
ብትደበዝዝ እንጂ እውነት ጠፍታ አታውቅም:: (2x)